# <u>የተፈጥሮ ገመድ</u>



የኖረ፣ የቆየም፣ ክጥንት በተፈጥሮ
ብልጥ ናት እንበል፣ ወይ ሞኚት፣ ተላላ
“ሰላም አውለኝ!” ስትል አንኮይቱ ወይዘሮ
በማለዳ ወጣች ልጇን አንጠልጥላ
ቅጠል ስትሸመጥጥ ጦጢትዋ ዝንጀሮ
ከአንዱ ዛፍ ሌላ ዛፍ ስትዘልል ውላ…

ከሞቀ ጉድጓዱ ያላንዳች ጕርባጣ
ከሚስት፣ ከልጆቹ ተደራርቦ አድሮ
ማለዳ ወጋገን ከደጅ ሲወጣ
ፊቱን እያሻሸ ቀልጣፋው ቀበሮ
“አምላኬ ምሳዬ ወደኔ እንዲመጣ
አደራ እንዳይዘገይ፣ ሰዓቱም ተከብሮ…



“ላክልኝ አምላኬ አንዲት ጠቦት ጠጣ!”
ብሎ ይለምናል ምሳውን ሊበላ።
በዳገቱም መንገድ፣ ከአባጣ፣ ጐባጣ
ድንገት ተገናኙ ተኩላና ድኩላ
ተራው ከደረሰ ማን ከሞት ሊያወጣ!
ሁሉም ቀጠሮ አለው የተፈጥሮ መላ



የጦጢቱም ግልገል አጉል ሲቦርቅ
ሮጦ፣ ሲወራጭ፣ ሲዘልል እንደ ጥጃ
ተደብቆ ነበር ቀበሮው ሊነጥቅ
ነጫጭ ጥርሶቹን ስሎ እንደ ሳንጃ
ግልገሉም አላየው እንጣጥ ብሎ ሲወድቅ
አንቆት ጭልጥ አለ ያለአንጃ ግራንጃ

ተኩላም እንደ እናት ልጅ፣ የድኩላ ወዳጅ
ገና ከሩቅ አይቶት መስሎ ዘመድ አዝማድ
ተጠመጠመበት ድንገት ሳይዘጋጅ
አንገቱንም አንቆ ሳም፣ ሳም በግድ
ቡጭቅጭቅ፣ ብጥስጥስ፣ የቄራ አራጅ
ኣይ አጉል ቀጠሮ፣ አጉል መዋደድ!



በተፈጥሮ ገመድ ሁሉም ተሳስረው
ቀጠሮን ከማክበር አይተላለፉም
አዳኝና ታዳኝ ፈርተው፣ ተከባብረው
ምን ቀኑ ቢረዝም ከሞት'ኮ ኣይተርፉም
ይኸ ነው ምስጢሩ፣ የዓለም ተፈጥሮው
ሟችን እስኪያገኙ ገዳዩች አያርፉም…

ገ/ኢ. ጐርፉ።